# የደንካራው ሰው
# ፍጹም መለወጥ



በአማኑኤል እንዳለ

**ማውጫ** **ገፅ**

መግቢያ ..... 3
**ክፍል አንድ** ..... 6
**ኀጢአት ምንድነው ?** ..... 6
**የብሉይ መጽሐፍት ምስክርነት** ..... 6
**ኦሪት ዘፍጥረት 6፡5** ..... 6
**ኦሪት ዘፍጥረት 8፡21** ..... 7
**የአዲስ ኪዳን ምስክርነት** ..... 9
**ሮሜ 2፡17-24** ..... 9
**ሮሜ 1፡18-21** ..... 9
**ኤፌ 2፡1-5** ..... 9
**የማርቆስ ወንጌል 7፡20-23** ..... 10
**ክፍል ሁለት** ..... 12
**2.1 የኀጢአት አለም አቀፋዊነት** ..... 12
**2.2 የውርስ ኀጢአት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ** ..... 13
**2.3 የውርስ ኀጢአት በመጽሐፍ ቅዱስ** ..... 15
**ክፍል ሦስት** ..... 19
**ዳግም ውልደት** ..... 19
**የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ምስክርነት** ..... 19
**ትንቢተ ኤርሚያስ 31፡31-36** ..... 19
**ትንቢተ ሕዝቄል 11፡19-20** ..... 20
**የአዲስ ኪዳን ምስክርነት** ..... 22
**ዮሐንስ 1፡11-13** ..... 22
**ዮሐንስ ወንጌል 3፡5-8** ..... 23
**ኤፌሶን 2፡4-6** ..... 25
**ክፍል አራት** ..... 27
**እግዚአብሔር አድልዎ ያደርጋልን?** ..... 27

# ምሥጋና

በመጀመሪያ በእኔ መፈለግን እና ማድረግን በመንፈሱ  ለሚሰራ ታላቅ አምላክ እግዚአብሔር ይሁን። በሆሄ እርማት ያገዘኝ ታናሽ ወንድሜን ኤፍሬም እንዳለ እግዚአብሔር ይባርክህ ለማለት እወዳለው።

## መታሰቢያነቱ

ይህች ትንሽ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ በየቦታው በተሀድሶአዊ እምነት ምክንያት የተለያዩ መከራን እየተቀበሉ ላሉ ወንድሞች በሙሉ ትሁንልኝ።

## መግቢያ

ይህ ትንሽ መጽሐፍ በነገረ ድነት ጥናት ውስጥ በኀጢአቱ እና በበደሉ ምክንያት ፍጹም ከእግዚአብሔር ሁለንተና የተለየው ሰው ዳግም ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለማድረግ ያለ መንፈስ ቅዱስ ስራ በንስሐ ሊመለስ እና የእግዚአብሔርን በረከት ሊካፈል እንደማይችል ለመሞገት የቀረበ አጭር ጽሁፍ ነው።

አንዳንድ ወገኖች በዚህ ርዕስ በተለይም በፌስቡክ በቅዱሳት መጽሐፍት እና ጥንታዊ በሆኑ የክርስትና አስተምህሮዎች ላይ (ጥንተ አብሶ ትምህርት፣ ዳግም ልደት፣ውጤታማ ጥሪ እና የሰው ሁለንተናዊ ደንካራነት) በማወቅም ይሁን ባለማወቅም ስሁት ትምህርታቸውን እውነት አስመስሎ በማቅረብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋርም ሆነ እርስ በእርሱ በሚጋጭ መልኩ ደህንነታችን በእግዚአብሔር ጸጋ የተፈጸመ መሆኑን ክደው ወንድሞችንም ለማሳት ደፋ ቀና ሲሉ በመመልከቴ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነታ ላቀርብ እንዲሁም ጥያቄዎችን ላነሳ ጥያቄዎችንም በዚሁ ጽሁፍ ለመመለስ ጥረት አደርጋለው።

በዚህ ውስጥ ምን አልባት ስህተት ቢገኝ በማንኛውም መንገድ የሆነን ቡድን የሚያስፈርጅ ሳይሆን ሙሉ ሀላፊነቱ የእኔ የጸሐፊው መሆኑን አስቀድሜ ላሳውቅ እወዳለው።

በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ዓመተ ምህረቶች እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።

የተጠቀምኩት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ አዲሱ መደበኛ ትርጉምና የ1954 ዓ.ም ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ።

ይህ ጽሁፍ በአጠቃላይ ሶስት ነገሮች ላይ ተመስርቶ አጠቃላይ ርዕሱን ያደራጃል እነዚህም ርዕሶች

- ኀጢአት ምንድነው ?
- የኀጢአት አለም አቀፋዊነት እና የውርስ ኀጢአት
- ዳግም ልደት ወይስ እምነት
- በእግዚአብሔር ዘንድ አድልዎ ያደርጋልን? በመጽሐፍ ቅዱስ እና በአመክንዮ
- ጥያቄ ለአርሚኖሳዊያን ወገኖች

ይህንን መጽሐፍ ለማጥናት ሆነ ሌሎች ሰዎች እንዲያነቡት ማጋራት ወደው በብዛት ኮፒ ለማድረግ ቢፈልጉ አስቀድመው ከጸሐፊው ፈቃድ መጠየቅ ይገባል።

# ክፍል አንድ

## ኀጢአት ምንድነው ?

ኀጢአት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሕገ እግዚአብሔርን መተላለፍ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ይህ ማለት እግዚአብሔር በቃሉ በኩል አንደኛ አድርጉ ያለንን ነገር ባለ ማድረግ አታድርጉ ያለንን ደግሞ በማድረግ ውስጥ በእነዚህ በሁለቱ ኀጢአት ከሕገ እግዚአብሔር ተላላፊ ሆኖ መገኘት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ዮሐ 3፡4 ዘዳ 9፡7 ኢያሱ 1፡18)።

በእነዚህ ምንባባት ውስጥ የምንረዳው ነገር ሐጢአት ሰዎች ከሚሰሩት ስራ ጋር የተቆራኘ መሆኑን ፡ማለትም በሕገ እግዚአብሔር የተገለጡትን በመተላለፍ የሚገለጥ የሰዎች ድርጊት መሆኑን ነው።

ሌላኛው የኀጢአት ትርጉም ደግሞ አመጻ ማለት ነው። ሰዎች የሚሰሩት ማንኛውም ኀጢአት እግዚአብሔር ላይ የሚሆን አመጻ ነው። ዓመጽ የሚለው ቃል ከሕገ እግዚአብሔር ተላላፊ መሆንን ብቻ ሳይሆን ወደ መሃሪው ጌታ አለመመለስ እና እግዚአብሔርን መበደል ነው። (መዝ 51፡5) አመጽ በደል ከማድረስ ጋር አንድ አይነት ትርጉም አለው። ለምሳሌ በዚህ ምንባብ ዳዊት ኀጢአቱን ለእግዚአብሔር ሲናዘዝ አንድ ጊዜ የተደረገ ሳይሆን የታቀደ እና የተደጋገም እንደሆነ አድርጎ እራሱን በማቅረብ የሰራውን ኀጢአት ይናገራል።

ከላይ ባየናቸው ሁለት ትርጉም ውስጥ ስለ ኀጢአት መሰረታዊ ነገር የምንረዳው ነገር ኀጢአት ሕገ እግዚአብሔርን ተላላፊ ከመሆን ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው።

ሌላኛው መጽሐፍ ቅዱስ ሐጢአትን የሚያቀርብበት መንገድ ደግሞ ከድርጊት የቀደመ የልብ ዝንባሌ ሆኖ ነው።

እስቲ ይህንን በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን እንመልከት። ሰዎች ሐጢአትን ለምን ይሰራሉ?  ብለን ለምንጠይቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሚረዳን ይሆናል።

### የብሉይ መጽሐፍት ምስክርነት

<u>**ኦሪት ዘፍጥረት** 6፡5</u>

በዚህ የብሉይ መጽሐፍ በዘፍጥረት ምዕራፍ ስድስት ቁጥር አንድ ላይ በስድስተኛው ቀን የተፈጠረው ክቡር ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ከአንድ ምዕራፍ የዘለለ ሕብረት ማድረግ አልቻለም ነበር። በዘፍ 1፡26 አፈጣጠሩን ይነግረናል በሁለተኛው ምዕራፍ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ሲያደርግ ይታይና በሶስተኛም ምዕራፍ በእግዚአብሔር ላይ በማመጹ ምክንያት ከእግዚአብሔር ይለያል። ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች ውብ ሆነው ተመለከቷቸውና ከእነርሱ መካከል መርጠው እንዳገቡ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

በእርግጥ በመጀምሪያው ቁጥሮች ላይ ያለው ነገር ምንነት ለመተንተን እጅግ ሰፊ እና ከርዕሳችን ውጪ ስለሆነ ምንድነው ?እነማን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው እንተውና ወደ ቁጥር አምስት እንመልከት።

> [5] The LORD saw that the wickedness of humankind was great in the earth, and that was a great in the earth, and that every inclination (imagination,

Intention,) of the thoughts of their hearts was only evil continually. Gen 6፡5 NRSV

እግዚአብሔር የሰዎችን ድርጊት ብቻ ሳይሆን የልባቸውንም አዘንብሎት የሚያይ ከድርጊት በፊት የልብን ሃሳብ አስቀድሞ አውቆ ስለ ድርጊት ሳይሆን ልብ ውስጥ ስላለ ሐሳብ ሰዎችን ሐጢአተኞች ይላቸዋል።

እግዚአብሔር የሰዎችን የልብ ሀሳብ እንደሚመርምር መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርባቸው ቦታዎች:-ዘዳ 31፡21 1ዜና 28፡9 29፡18

ስለዚህ በዚህ ቦታ እግዚአብሔር አምላክ ሰዎች በምድር ላይ ምን ያክል በደለኞች እንደሆኑ መመልከትቱን ብቻ ሳይሆን ዘውትር አዘንብሎታቸው ወደ ክፉ በመሆኑ የጥፋት ውሃን በማምጣት ሊቀጣቸው መወሰኑን እናስተዉላለን።

**<u>ኦሪት ዘፍጥረት</u>** <u>8፡21</u>

ከፍ ባለው ምንባብ ውስጥ የልቡ ሐሳብ ተብሎ የተገለጠው ቃል አሁንም በድጋሚ ዘፍ 8፡21 ከጥፋት ውሃ ከተረፉት ኖህ ጋር እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሲገባ ስለ ሰው ልጅ የልብ ሁኔታ በዘፍጥረት ምዕራፍ ስድስት ጋር ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ቃል (יֵ֫צֶר **yetser)** ይጠቀማል በዚህም ቦታ ያለው ሀሳብ ከቀደመው ጋር አንድ አይነት ነው።

[21] And when the LORD smelled the pleasing order, the LORD said in his heart, “I will never again curse the ground because of humankind, for the inclination of the human heart is evil from youth; now will I ever again destroy every living creature as I have done. Gen 8፡21 NRSV

በዚህ ቦታ ልክ እንደከዚህ ቀደሙ የሰው የሐጢአት ተጠያቂነት በሚያደርገው ነገር ላይ ብቻ ሳይሆን ሁሉን በሚያቅ አምላክ ፊት የልቡ ሁኔታን በመመዘንም ጭምር ነው። ይህ ክፋት ከየት እንደሚጀምር ሲናገር እዚህ ቦታ ላይ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከልጅነቱ በማለት ሲገልጽ የ1954 ትርጉም ደግሞ ከታናሽነቱ በማለት ይህ የልቡ አዘንብሎት ከልጅነት ጀምሮ ወደ ክፉ እንደሆነ ይናገራል።

ምንም ሰዎች መሠረታዊ የሆነው የልባቸው ሁኔታ ባይለወጥም እግዚአብሔር ግን ደግሞ ምድርን ስለ ሰው ልጅ ኀጢአት እንደማያጠፋ ቃል ገባ ማለት ነው።

ስለዚህ ኀጢአተኝነት በእግዚአብሔር ፊት ከድርጊት የቀደመ ነው። ምክንያቱም እርሱ ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ነውና።

አንድ የመጨረሻ የብሉይ መጽሐፍ ምንባብ እንመልከት እና የብሉይ ዳሰሳችንን እናጠቃልል

## **ትንቢተ ኤርሚያስ 17፡9**

የይሁዳ ቤት በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ በራሳቸው ጉልበት ሲታመኑ በዚህም እግዚአብሔር የይሁዳን ቤት ሲወቅስ በኤርሚያስ በኩል የተነገረ ቃል ነው። በእግዚአብሔር ስለማይታመኑ እና በራሳቸው ስለሚታመኑ መዝሙረኛው በመጀመሪያው ምዕራፍ ከገለጸው ጋር በሚመሳሰል መንገድ ይሁዳ ስለሚጠብቀው ቅጣት በምሳሌ ኤርሚያስ ይናገራል (ቁ-5-6) እንዲሁም በእግዚአብሔር ስለሚታመኑ ደግሞ በቀጣይ ቁጥር (7-8) ይናገራል።

> [9] The heart is devious above all else; it is perverse --- who can understand it? Jer 17:9 NRSV

በዚህም ስፍራ ነቢዩ ኤርሚያስ ስለ ሰው ልብ ተመሳሳይ ነገር ይናገራል በእግዚአብሔር ላይ ባለመታመናቸው የሚወቀሱት የይሁዳ ቤት ሐጢአታቸው ከዚህ ክፉ ከሆነ ልብ የወጣ እንደሆነ ያመለክታል።

ነቢዩ ኤርሚያስ በዚህ ስፍራ ልክ ከላይ በዘፍጥረት ምዕራፍ ስድስት ላይ ያለውን የ ኒው ሊቪንግ ትራንዝሌሽን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ እንደሚናገረው

> [Now Lord observed the extent of the people’s wickedness] Gen 6፡5 NLT

የሰው ልጅ ልብ ውስጥ ስላለው ሐጢአት ጥግ ይናገራል። በማወዳደርም በምድር ካሉ ክፉ ነገሮች ይልቅ የሰው ልብ እጅግ ክፍ እና ተንኮለኛ እንደሆነ ይናገራል።

የሰው መሰረታዊ ችግሩ ልብ ጋር እንደሆነ በእነዚህ ምንባባት ልናስተውል እንችላለን። እግዚአብሔር የሰዎችን ድርጊት ሆነ ድርጊቱ ሚፈልቅበት ልብ ይመረምራል በዚህም ” የሰውን ልብ ክፋት ጥልቀት እግዚአብሔር ካልሆነ ማን ሊረዳው ይችላል?” በማለት ይጠይቃል።

> ተመሳሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት [መክ 9፡3 ኤር 16፡12 ኤር 11፡8]

## የአዲስ ኪዳን ምስክርነት

አዲስ ኪዳን ኀጢአትን ከሰዎች ድርጊት ጋር አያይዞ አመጽ እና በደል በሚለው ትርጉም መሰረት ሰዎችን ሕገ እግዚአብሔርን ተላላፊዎች አድርጎ በማቅረብ በዚህም ምክንያት ሐጢአተኞች እንደሆኑ ይናገራል።

**ሮሜ** 2፡17-24

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ሕግ የተሰጣቸውን አይሁዳዊያንን በሚመለከት የሚነገረን ነገር ቢኖር ምንም ሕጉ አትስረቅ ቢልም ሌቦች በመሆን አታመንዝር ቢልም እንኳን እነርሱ ግን አመንዝራዎች አሕዛብን "ጣዖት አምላኪዎች" በማለት የሚሳደቡ ራሳቸው ግን ቤተ መቅድስ መዝባሪዎች በመሆናቸው አይሁዳዊያንን ሕግ ተላላፊዎች ሲል ይጠራቸዋል።

**ሮሜ** 1፡18-21

በዚህ ምንባብ ውስጥ ደግሞ ከአይሁድ ውጪ የሆኑትን አሕዛብን በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ ይናገራል። ምንም ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚገባውም ነገር ለእነርሱ በፍጥረት ምስክርነት በኩል ግልጽ ቢያደርግም አህዛብ ግን መልሰው ፍጡርን አመለኩ። አምላኮቻቸውንም በእጆቻቸው አበጁ።

አንድ አምላክ እግዚአብሔር ቢኖር በከንቱነት የራሳቸውን አማልክት አበጁ በዚህም ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ ኀጢአትን እንደሰሩ እና ሕገ እግዚአብሔርን ተላላፊዎች እንደሆኑ ይናገራል።

**ኤፌ** 2፡1-5

ይህ ክፍል ሁላችንም በእጃችን በምናገኘው አዲሱ መደበኛ ትርጉም የተሰጠው ኀይለ ቃል በክርስቶስ ሕያው መሆን የሚል ነው በዚህ ኀይለ ቃል ውስጥ ደግሞ ከቁጥር አንድ እስከ አስር ድረስ ያለው ተካቶ ቀርቧል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ስለነበሩበት መንፈሳዊ ሁኔታ ሲናገር በሀላፊ ጊዜ አመልካች ነው እናንተ በበደላችሁና በሐጢአታችሁ ምክንያት ሙታን ነበራችሁ በማለት ይናገራል። በመቀጠል እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ እርሱም ቢሆን ሐዋርያው ጳውሎስ እራሱን በማካተት እኛ ሁላችን በማለት እርሱም በክርስቶስ ሕያው የሆነ ሙት እንደነበር ይናገራል።

### ለመሆኑ ሙታን ነበራችሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሙታን የመሆን ትርጉም በዚህ በኤፌሶን ምዕራፍ ሁለት አውድ እነዚህ ሆኖ ሊተረጎም ይችላል

እኛ በእግዚአብሔር ሐይል ሕያዋን ሆነን በፊቱ መመላለስ ከመጀምራችን አስቀድሞ የነበረንን ምልልስ ሙታን መሆን ብለን ልንተረጉም ይገባል ብዬ አምናለው። አስቀድመን ስንከተል የነበረው የዓለምን ክፉ መንገድ ነበር (ቁ-2) እግዚአብሔርን በማይታዘዙ አመጸኞች ላይ ለሚሰራው ለዛውም መንፈስ የምንታዘዝ (ቁ-2) የስጋችንን ምኞዐት እያረካን የምንኖር የነበርን (ቁ-3) ልክ እግዚአብሔር የማይታዘዙትን እንደሚቁጣባቸው እኛም የቁጣ ልጆች ነበርን።

እዚህ ጋር በቁ-3 ላይ "ምኞት" የሚለው θέλημα **thelema** (thel'-ay-mah) ይህ የግሪክ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ 64 ጊዜ ሲጠቀስ አብዛኛውን (62) ጊዜ ከፈቃድ ጋር ተያይዞ ትርጉም ላይ ሲውል ለምሳሌ "ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች (ማቴ 6፡10) በሚለው ቦታ ላይ ፈቃድ ጋር ተያይዞ ተተርጉሟል። እንደገናም የዚህ ቃል ትርጉም አንድ ጊዜ ምኞት የሚል ትርጉም ይዞ በዚህ በኤፌሶን ብቻ ቀርቧል።

ስለዚህ ልባችን ውስጥ ያለውን ክፋት ደግሞ ስንፈጽም ስለነበረበት ሁኔታ ሲናገር “እያረካን” በማለት ይገልጻል። ስንፈጽም የነበረው እጅግ በእብሪተኝነት በመታበይ በደስታ ነበር።

በኤፌሶን ሁለት ኅጢአት ሲተረጉም ለሰይጣን መታዘዝ ሐጢአትን በፍጹም ደስተኝነት በደስታ ስሜት በማድረግ መመላለስ ሲሆን በዚህም ምክኒያት ሙታን ነበራችሁ ይለናል።

እዚህ ጋር እየተወራ ያለው ምን ዓይነት ሙታንነት እንደሆነ ግልጽ ነው። ከእግዚአብሔር ያለንን ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ ማጣት ነው። በዚህም በሐጢአታችን የምናፍር ሳይሆን እንዲያውም በደስታ እና በእርካታ የምንፈጽም የቁጣ ልጆች የነበርን ነን።

ከልባችን ሁኔታ እስከ ምልልሳችን ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር የተለያየ ለመንፈሳዊ ነገር ሳይሆን ለሐጢአት የሆነ እርካታ ያለን ነበርን በማለት ያናገራል።

በተጨማሪም እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ይመልከቱ ፦ [ሮሜ 3፡10-18 ቆላ 2፡13 ገላ 5፡19-21 ማቴ 15፡29]

እነዚህ ምንባባት እንደሚያስተምሩን ከሆነ ሐጢአት ማለት በድርጊት የታጀበ ሕገ እግዚአብሔርን ተላላፊ መሆን ነው። ይህን ከብሉይ ምንባባት ጋር ስሙም የሆነ አረዳድ ነው።

ነገር ግን ሐጢአት በአዲስ ኪዳን በልብ ያለ ማንኛውም ክፉ አዘንብሎት ተደርጎ ተወስዷል ለምሳሌ በአንቀጸ ብጹዐን ላይ በተራራው ስብከት ጌታ ኢየሱስ በማቲዮስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት ቁጥር 27 ላይ ማመንዘር ማለት አካላዊ በሆነ መንገድ የሚደረግ ከጋብቻ ውጪ የሆነ ሩካቤ ስጋ ብቻ ሳይሆን ሴትን በምኞት መመልከት እራሱ በጌታ ፊት አመንዝራነት እንደሆነ በመናገር እግዚአብሔር ድርጊትን ብቻ ሳይሆን ልብን የሚመረምር በመሆኑ ልባችን ንጹህ እንዲሆን አስተምሮናል።

## **<u>የማርቆስ ወንጌል</u>** 7፡20-23

በዚህ ምንባብ ውስጥ ፈሪሳዊያን እና ጸሐፍት ወደ እርሱ በመቅረብ ደቀ መዛሙርትህ የአባቶችን ወግ ተላላፊ ሆነዋል ሐጢአተኞች ሆነዋል በማለት ጌታችንን የሐጢአተኞች መምህር ለማድረግ ደቀ መዛሙርትን ወቀሱ።

ጌታም እነዚህን ፈሪሳዊያንን እና ጸሐፍትን ከትንቢተ ኢሳያስ በመጥቀስ ከንተ በሆነ ሰው ሰራሽ ትምህርታቸውን በመከተል ለሕገ እግዚአብሔር ግን ተላላፊዎች እንደሆኑ ወቀሳቸው (ቁ-6-9)

ሐጢአት ድርጊት ብቻ አለመሆኑን ጌታ ኢየሱስ በሚደነቅ መንገድ አስተማረ። እንዲህም በማለት ከሰው የሚወጣ ያ ሰውን ያረክሰዋል በማለት ሰዎች የሚረክሱት ከውስጣቸው ከሚወጣ ነገር ነው። ለመሆኑ ይህ ምን ማለት ነው?

ቀደም ብለን ባየናቸው የብሉይ ምንባባት ውስጥ የሰው ልብ የክፋት ምንጭ እንደሆነ ተረድተናል ይህኑኑ ጌታ ኢየሱስ እንደገና በግላጭ ሲናገር ከሰው ልብ የሚወጣ በማለት ሰዎች የሚረክሱበት ነገር ውስጣቸው ያለ ሲሆን እነዚህን ሲዘረዝር ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝርና፣ስርቆት፣ሰው መግደል፣ዝሙት መስገብገብ፣ ክፋት ማታለል፣መዳራት ምቀኛነት፣ ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው።

ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ከእኛ ልብ ውስጥ ይወጣሉ ማለት ነው።

እስከ አሁን የመጣነውን ነገር እናጠቃልል። በመጀምሪያ ትልቁ ችግር ኃጢአት ነው። የዚህ ትልቅ ችግር ምንጭ ደግሞ ልብ ነው። ስለዚህ ከዚህ ታላቅ ችግር ሰዎች ነጻ እንዲወጡ ልባቸው ሊቀየር ይገባል። ያ ካልሆነ ሰው እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ሊታረቅ ይችላል? ሰው ከውስጡ በሚወጣው ሐይል ስሜቱ በደስታ ኃጢአትን የሚያድረግ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲስማማ ፍጹም መለወጥ የሚገባው ልቡ ነው።

# ክፍል ሁለት

## 2.1 የኀጢአት አለም አቀፋዊነት

የኀጢአት አለም አቀፋዊነት ማለት ከላይ ባየነው የኀጢአት ትርጉም ውስጥ ሰው ሁሉ ሕግ ተላላፊ መሆኑን የሚያስተምር የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ነው።

ዳዊት በመዝሙሩ (መዝ 14፡2) እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ምድር ከሰው ልጆች መካከል የሚያስተውል እግዚአብሔርን የሚፈልግ መኖሩን ለማየት ተመለከተ ካለ በኋላ ውጤቱን ሲናገር ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል በማለት ኀጢአተኝነት አለም አቀፋዊ መሆኑን በዚህም ሰዎች በአንድነት የተበላሹ እንደሆኑ ዳዊት ተናገረ።

እንዲሁም ጠቢቡ ሰለሞን ትክክለኛ ነገር በእግዚአብሔር ፊት የሚያደርግና ሐጢአት የማይሰራ ጻዲቅ ሰው እንደሌለ ይናገራል (መክ 7፡20) ።

ሰለሞን በቤተ መቅደሱ ምርቃት ላይ ሲጸልይ ይህንን እውነት ያጠናክራል "መቼም ሐጢአት የማይሰራ የለምና" በማለት ሁሉም ሰው ሐጢአተኛ እና ከዚህም ውጪ የሆነው አንድ እንኳን እንደሌለ ይናገራል።

በተጨማሪ እነዚህን የብሉይ መጽሐፍ ቅዱሳትን ይመልከቱ [1ኛ ነገስት 8፡46 መዝ 143፡2 ምሳሌ 20፡9 ኢዮብ 15፡14 14፡1 2ዜና 6፡36]

የአዲስ ኪዳንም የሐጢአት አለም አቀፋዊነትን የሚደግፍ ነው ሮሜ ምዕራፍ 3 ቁጥር 9 ጀምሮ ባለው ምንባብ ሰው ሁሉ ሕገ እግዚአብሔርን ተላላፊ መሆኑን የአዲስ ኪዳን ምንባብ ያረጋግጣል ይህንም በተመለከተ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ በማለት አለም አቀፋዊ ይዘቱን አጽንዖት በመስጠት ሁሉም ከሐጢአት በታች መሆናቸውን ይደነግጋል። በ 23ተኛ ቁጥር በድጋሚ ሁሉም ሐጢአትን ሰርተዋል በማለት ያጠናክራል።

የሐጢአት አለም አቀፋዊነት ከአዳም ውድቀት ጋር በተገናኘ ሰዎች በሞላ እንዴት ሐጢአተኞች እንደሆኑ ሲናገር በውክልና ማለትም በአንዱ አዳም መተላለፍ ሁላችንም ሐጢአተኞች ሆነን እንደተቆጠርን የሚናገርበት ምንባብ ፦

**(ሮሜ 5፡12-14)**
"በአንድ ሰው ምክንያት ሐጢአት ወደ ዓለም ገባ" የሚለውን ይህንን የቅዱስ ጳውሎስ ንግግር ለመረዳት አዳም እንዴት አዳም እንደወከለን በሁለት መንገድ እንመልከት።

እግዚአብሔር ከአዳም ጋር በዘፍ 1፡26-30 እና ዘፍ 2፡16-17 መፍጠሩ እና የገባውን ቃል ኪዳን በተመለከተ እንደሚከተለው ቀርቧል

- ሰው (ወንድ እና ሴት) በእግዚአብሔር መልክ መፈጠሩ
- እንስሳትን በሙሉ እንዲገዛ
- እንዲባዛ እና ምድርን እንዲሞላ

እነዚህ ቃል ኪዳኖች ሁሉ ግን እንዲጸኑ በዔደን ገነት መካከል ካሉት ዛፎች መልካሙንና ክፉን ከሚያስታውቀው ውጪ ሁሉን እንዲበሉ ይህንን በበሉ ቀን ግን ሞትን እንደሚሞቱ ተናገረ ስለዚህ ከላይ የተገባላቸው ኪዳን እንዲሆንላቸው እንዲታዘዙ እግዚአብሔር አምላክ አዘዛቸው (ዘፍ 2፡8-9) ።

ይሁን እንጂ ሰው ይህንን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣስ በእግዚአብሔር ፊት ተረገመ እርግማኑ እንዲህ ቀርቧል (ዘፍ 2፡16-20)

- ሴት ልጅ በእርግዝናዋ ወራት ጭንቀት ይበዛባታል።
- ፍላጎቷ ወደ ባልዋ ይሆናል (በሐይል መገዛት)።
- ምድር የተረገመች ሆነች።
- ብርቱ ድካም።
- ምድር እሾህና አሜኬላ የምታበቅል ሆነች።
- የስጋ ሞት እንዲሞት ተወሰነ።

ነገር ግን እዚህ ጋር ልብ ልንል የሚገባን ነገር ከሰው ውድቀት ማግስት እግዚአብሔር ለእባቡ የተናገረውን በማስተዋል ሌላ መጣዒ ኪዳን እንደገባ ነው።

በእባቡና በሴቲቱ በዘሩና በእርሷ ዘር መካከል የዘላለም ጦርነት የሴቲቱ ዘር የእባቡን ዘር አናት ሲረግጥ እባቡ ደግሞ የሴቲቱን ዘር ተረከዝ የሜቀጠቅጥ ሆኖ እንደሚኖር የኋላ ኋላ ግን ድሉ የሴቲቱ ዘር የሚወክለው እርሱ እንደሚሆን ተናገረ።

ወደ ተነሳንበት ሐሳብ ስንመለስ ዘፍጥረት የአዳምንም የክርስቶስን ውክልና በግልጽ የተዘገበበት መጽሐፍ ነው። አዳም የሰው ልጆችን ወክሎ በመቆሙ በእግዚአብሔር ፊት ከሰው የሚወለድ ሁሉ ኀጢአተኛ ሆነው እንዲወለዱ ምክንያት ሆነላቸው።

ስለዚህ አዳም የሰውን ዘር ሁሉ ወክሎአል ስለዚህ ሰው ሁሉ በወከለው አዳም ምክንያት ኀጢአተኛ ነው ማለት ነው።

## 2.2 የውርስ ኀጢአት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ

የውርስ ኀጢአት ሁላችን ከአዳም የወረስነውን ሐጢአተኛ ተፈጥሮ እና እንዲሁም በደለኝነት የሚመለከት ነው። በዚህ ውስጥ የምንመለከተው ዋናው ነገር በአዳም መተላለፍ የሰው ልጆች ተፈጥሮ ላይ ያመጣውን ተጽዕኖ እና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት የምናጠና ይሆናል።

ይህንን ርዕስ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሶስት ከፋፍለን ልንመለከት እንችላለን

### ጴላጂያሳዊነት

- ይህ አመለካከት በአዳም ምክንያት ሰው ምንም አይነት ከአዳም የመጣ ምንም አይነት ሐጢአት የለም አዳምም መጥፎ ምሳሌ ከመሆን ውጪ በሰው ተፈጥሮ ላይ ለተከታዮቹ ምንም አይነት የተፈጥሮ መበላሸት ተጠያቂ አይደለም።
- ሰው ሲፈጠር ንጹህ ስለሆነ ሲፈልግ ሐጢአት ሊሰራ ካልፈለገ ደግሞ ጽድቅን ሊሰራ በራሱ ፍጹም ብቃት ያለው ፍጡር ነው።
- ስው ፍጹም ነጻ የሆነ ፈቃድ ያለው ፍጡር ስለሆነ ምንም አይነት የእግዚአብሔር ጸጋ ሳያስፈልገው በራሱ መዳንን ሊያደርግ የሚችል ነው።

ጴላጂየስ የኢንግሊዝ መነኩሴ እንደሆነ ይነገርለታል በእርግጥ አንዳንድ የታሪክ ሙሁራን ይህን ቢያስተባብሉም ከእንግሊዝ ወደ ታላቁ ሮም በመምጣቱ በጊዜው በነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ወደ አውግስጢኖስ ከተማ ሂፖ በማቅናት በከተማው የነበሩ ክርስቲያኖች ያላቸውን የክርስትና ሕይወት ሲመለከት እጅግ በጣም ፈር የለቀቀ ነበር። ታዲያ በጊዜው እጅግ ተደማጭ የነበረው የሂፖው ቢሾፕ ቅዱስ አውግስጢኖስ የሚያስተምረው ትምህርት ለዚህ የክርስቲያኖች ሕይወት መበላሸት ምክንያት እንደሆነ በማንሰብ ሌላ ትምህርት ጀመረ ትምህርቱንም ከላይ በአጭሩ አስቀምጫለው።

**አውግስጢኖሳዊነት**

ቅዱስ አውግስጢኖስ የሚያስተምረው ትምህርት በአጭር ሲቀርብ

- የአዳም ሐጢአት አዳምን ብቻ የጎዳ ሳይሆን ሰዎች በሞላ ኀጢአተኛን ተፈጥሮ ይዘው እንዲወለዱ ሆኗል (መዝ 51፡5)
- ሰው ከሕጻንነቱ ጀምሮ ወደ ክፉ ካዘነበለ ሐጢአተኛ ልብ ጋር በመወለዱ "ነጻ ነው" የሚለውን የጴላጀየስን ትምህርት ተቃወመ።
- ሰው የሐጢአት ባሪያ ነው (ዮሐ 8፡34) ስለዚህ ሰው በፈቃዱ ሊያደርግ የሚችለው ባሪያ አድርጎ የያዘውን ነገር ነው ይህም ሰው የሐጢአት ባሪያ ስለሆነ መስራት የሚችለውም ሐጢአት ብቻ ነው።
- ሰው ባሪያ ስለሆነ በራሱ ፈቃድ ሊድን አይችልም (ዮሐ 6፡44) አብ ሊሰበው ግድ ያስፈልገዋል።

ቅዱስ አውግስጢኖስ (354-430 ዓ.ም)

**<u>የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ውስኔ</u>**

የኤፌሶኑ ጉባዔ (431 ዓ.ም)

የኤፌሶኑ ጉባኤ ሶስተኛው የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ሲሆን ከኒቂያው ጉባዔ (325 ዓ.ም) እና ከቁስጥንጢኒያው ጉባዔ (381 ዓ.ም) የቀጠለ ጉባዔ ነው።

በዚህ ጉባዔ ውስጥ በክርስቶስ ኢየሱስ ማንነት ላይ በኒስጥሮስ የተጀመረውን የስህተት ትምህርት በማውገዝ በቀጠል ደግሞ በጴላጂየስ እና በአውግጢኖስ መካከል የነበረውን ክርክር አድምጠው ጴላጀየስን በማቅገዝ የቅዱስ አውግጢኖስ ትምህርት ቀጥተኛ እና የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ትምህርት ሆኖ ቀጠል።

ይህ ብቻ ሳይሆን በሮሙ ሊቀ ጳጳስ ተወገዟል (417 ዓ.ም) በካርቴጁ ጉባዔ (417 ዓ.ም) በቤተ ክርስቲያን ተወገዘ።

ጥቂት ዓመታትን አልፎ ቤተ ክርስቲያን በጴላጀየስ የተጀመረው ኑፋቄ ዳግም በዮሐንስ ካሳሲያን ከጴላጀየስ በከፊል ትምህርቱን በመቀበል ያስተምር ጀመር

**ግማሽ ጴላጂየሳዊነት**

- ሰው የውርስ ሐጢአት እንዳለበት መቀበሉ ከጴላጀየስ ይለየዋል።
- ሰው ምንም የውርስ ሐጢአት ቢኖርበትም ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር ሊተባበር ይችላል።

- በእርግጥ ሐጢአተኞች ብንሆንም ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጸጋ ሊካፈል የሚችልበት አቅም አለው።
- አውግጢኖች የሚያስተምረውን አጠቃላይ ደንካራነት ግማሽ ደንካራነት (Partial depravity) በማለት አስተማረ።

**የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ምላሽ**

የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ በዮሐንስ ካሳሲየስ ላይ የውግዘት ብየና አስተላለፈ ይህም ጉባዔ የኦሬንጁ ጉባዔ በመባል ሲታወቅ ከላይ የተነሳው የግማሽ ጴላጂያሳዊነት ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ተወገዘ የካርቴጁ ጉባዔ እና የኤፌሶኑን ጉባዔ ላይ የተወገዘው ውግዘት በድጋሚ በካሳሲየስ ላይ ደረሰ። በዚህም በድጋሚ አውግጢሶናዊነት በቤተ ክርስቲያን ቀጠለ።

እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ታሪኮች የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ቢሆንም በተሀድሶ ወቅት ይህንኑ ትምህርት የተሀድሶ አባቶች ማለትም (ማርቲን ሉተር ኡሪክ ዙዊንግሊ እና ዮሐንስ ካልቪ) አውግሲጢሶናዊነትን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በፕሮቴስታን ቤተ ክርስቲያን ዛሬም እንዲቀጥሉ ሲያደርጉ በሆላንድ ከተማ ካልቪናዊ የነበረ ያዕቆብ አርመን ግማሽ ጴላጂየሳዊነትን ዳግም ብቅ ቢያደርግም ከህልፈቱ በኋላ በአርሜኖሳዊያን ተከታዮች እና በካልቪናዊያን መካከል በተደረገ ክርክር በዶርቱ ጉባዔ (1618-19 ዓ.ም) ተወገዙ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አውግስጢሶናዊነት ቀጠለ።

## 2.3 የውርስ ኀጢአት በመጽሐፍ ቅዱስ

የውርስ ኀጢአት ማለት ከስያሜው በቀላሉ እንደምንረዳው የተወረሰ ኀጢአት ማለት ነው። ከፍ ባለው ጥናታችን በአዳም ውክልና ውስጥ እኛም በእግዚአብሔር ፊት ሐጢአተኞች ሆነን እንደተቆጠርን የምንረዳበት የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ነው። በተለይም በሮሜ 5፡18 በአንድ ሰው መተላለፍ ኩነኔ በሰው ሁሉ ላይ እንደመጣ ይነግረናል። ቀጥሎም በአንድ ሰው አለመታዘዝ ማለትም አዳም በዘፍጥረት ሕገ እግዚአብሔርን ተላላፊ ሲሆን የሰው ዘር በሞላ በእግዚአብሔር ፊት በአንድነት ኀጢአተኞች መሆናችንን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ሮሜ 5፡18-19)።

ስለዚህ ምንም አዳም በዔደን ገነት በእግዚአብሔር ላይ ቢያምጽም ይህ አመጽ የሰው ልጆች ሁሉ ተደርጎ በመቆጠሩ ከፍጥረታቸው እግዚአብሔር ቁጣውን የሚገልጥባቸው እንደሆኑ በድጋሚ መጽሐፍ ያስተምራል (ኤፌ 2፡3)።

በዚህ ስፍራ ምን አልባት እኛ ስጋ ለባሾች እነዚህ ብለን እናስብ ይሆናል እኛ ባላደረግነው እንዴት የአዳም ሐጢአት ለእኛም ይቆጠራል? ብለን እንጠይቅ ይሆናል

ለዚህ ጥያቄ ዶክተር ዌይን ግሩደም ሶስት አማራጭ መለሶችን ያቀርባል

1. ምንም እግዚአብሔር ይህንን ሐጢአት እንኳን ባይቆጥርበትም እያንዳንዱ ሰው ሊቆጠርበት የሚችል ኀጢአት ይሰራል በዚህም ኀጢአተኞች እንሆናለን (ከላይ የሐጢአት መንስኤ ልብ እንደሆነ አይተናል) ሮሜ 2፡6 ቆላ 3፡25
2. እኛ እያንዳንዳችን በአዳም ቦታ ብንሆን ልንሰራ የምንችለው ኀጢአት ይኸው ነበር ይህንም የሚያረጋግጥ ዕለት ዕለት የምንሰራው ኀጢአት የሚታይ ነው (ይህ ግን ብዙም በዶክተር ዌይን ግሩደም ተቀባይነት የለውም)።

3. በዚህ ቦታ በአዳም መወከል አልነበረብኝም ማለት በክርስቶስ ኢየሱስ ስራ እኛ ተወክለን የክርስቶስ ጽድቅ ለእኛ ሊሆን አይገባም ወደሚል ድምዳሜ ያደርሰናል ይህም የእግዚአብሔር ጸጋን መቃወም ይሆንብናል።

በተራ ቁጥር ሶስት የቀረበው አማራጭ ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን በፈቃዱ ምክር የሚሰራ አምላክ ነው (ኤፌ 1፡11) ። አምላካችን ሉዐላዊ በመሆኑ የአዳም ሐጢአት በውክልና ለእኛም ሆኖ እንዲቆጠር አድርጎአል።

ደግሞም በክርስቶስ ኢየሱስ በመወከል የክርስቶስን ፍጹም መታዘዝ የእኛ መታዘዝ አድርጎ እኛን ከነበረብን የሐጢአት ባርነት ነጻ በማውጣት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ልጆች አድረገን። በዚህ ሁሉ ልብ ልንል የሚገባን ይህን ሁሉ በፈቃዱ ምክር የሚሰራ መሆኑን ነው።

### 1. የተወረሰ ብልሽት

ተያያዢ በሆነው ጥንታችን ውስጥ ልናስተውል የምንችለው ነገር ሐጢአት የሰው ልጅ ትልቁ ተግዳሮት፣ ከአምላኩ ያራቀው እና የእግዚአብሔር ጠላት የሆነበት ምክንያቱ ነው። ኀጢአት ፍጹም እግዚአብሔርን እንዲያከብር እና በእርሱም እንዲደሰት የተፈጠረውን ሰው ፍጹም ከአምላኩ እንዲለይና በሁለንተናው በአምላኩ ላይ እንዲያምጽ እንዳረገው አይተናል።

ሌላኛው የተረዳነው ነገር ደግሞ የሰው ልብ ምነኛ ተንኮለኛ እንደሆነ ነው። ይህም በተለይ በዘፍጥረት ምዕራፍ 5ና 6 ክፍሎች ውስጥ ባየናቸው ምንባብ ውስጥ ከልጅነቱ ወይም ከሕጻንነት ጀምሮ ልቡ ወደ ክፉ ያዘነበለ እነደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳችን ይናገራል። ስለዚህ በአሁኑ ጥናታችን የተወረሰ ብልሽት ብለን የምንጠራው ይህንኑ በኀጢአት ፍጹም የተበላሸ የመሆንን የውርስ ኀጢአት ሁለተኛው መገለጫን እናያለን።

የኀጢአት ተፈጥሮ ስንል ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምጹ መልካም የሆነውን ከማድረግ ይልቅ ክፋትን የሚፈልጉበት ምክንያት ነው። ለምሳሌ እዚህ ጋር ሕጻናትን ልንጠቅስ እንችላለን። ማንም ሕጻናትን ክፋት አያስተምርም ገና በሕጻንነት በእናቱ ጉያ ሆኖ ራስ ወዳድ ሆኖ እናያለን። ይህንን ለመረዳት ሕጻናት ከእናታቸው የሚያገኙትን የጡት ወተት በፍጹም ከእነርሱ ውጪ ሌላ ሕጻን እንዲወስድባቸው አይፈልጉም። ቢቻላቸው ጥቅማቸውን ለማስከበር አንደበታቸውን ወይም ሐይላቸውን ተጠቅመው በከለከሉ ነበር ነገር ግን ይህን ማድረግ ሰለማይችሉ በለቅሶ ጥቅማቸው ለማስከበር ራስ ወዳድነትን ይገልጻሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈላቸው መልዕክት ውስጥ (ሮሜ 8፡3) ከስጋ ባሕሪ የተንሳ ሕግ ሊፈጽም ያልቻለውን በማለት በአሮጌው ኪዳን ምንም ሕጉ ፍጹም እና ብርሃን ቢሆንም ሰዎች ከስጋ ባሕሪ የተነሳ ሊፈጽሙት ወይም ሊጠብቁት እንዳልቻሉ ይናገራል። እንዲሁም ወረድ በማለት የስጋ ባህሪ ማለት ምን እንደሆነ ደግሞ ሲያስረዳ (ቁ-7) ለሐጢአት የተገዛ አእምሮ ሲሆን በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ መሆን እና ለእግዚአብሔር ሕግ ሊገዛ አለመቻሉ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከስጋ ባሕሪ የተነሳ ልባችን በስጋ ፍላጎት ላይ የሚያርፍ (ቁ-5) በስጋን ነገር የሚሳብ (ቁ-6) ለሐጢአት ባሪያ የሆነ(ቁ-7) ለእግዚአብሔር ሕግ መገዛት የማይችል (7) እና በአጠቃላይ እግዚአብሔርን ማስደሰት የተሳነው መሆኑን ያስተምራል።

ይህ የወረሰነው የተበላሸ የኀጢአት ባሕሪይ በሁሉም ሰው ላይ ያለ ሲሆን እያንዳንዱ ግለሰብ በግሉ በሚያደርጉ ክፋት የሚገለጥ ነው።

በተጨማሪ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ይመልከቱ [ቆላ 3፡5 ሮሜ 7፡14 7፡25 7፡14 ኤፌ 4፡22 ገላ 6፡8]

መዝሙረኛው ዳዊት ደግሞ የኦሪዮን ሚስት ቤርሳቤህን ካስነወረ ኦሪዮንን ካስገደለ በኋላ ነቢዩ ናታን መጥቶ ኀጢአቱን ገልጦ ከተናገረ በኋላ ዳዊት ኀጢአተኛ መሆኑን በእግዚአብሔር ፊት በመናዘዝ እንዲህ ይላል

**መዝ 51፡5 "ስወለድ ጀምሮ ኀጢአተኛ በደለኛ ገና እናቴም ስትጸንሰኝ ጀምሮ ሐጢአተኛ ነኝ።"**

ዳዊት አጠቃላይ በእግዚአብሔር ላይ እየተናገረ ነው (ቁ-4) ። ኀጢአቱ ምን እንደሆነ ተረድቷል (ቁ-3)። በዚህም ዳዊት እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የሚያደርገው ነገር በሞላ ትክክል እና ጻዲቅ እንደሆነም ተረድቷል። (ቁ-4) ነገር ግን ዳዊት እግዚአብሔር ከኀጢአቱ እንዲያነጻው ይለምናል ።(ቁ-7) ስለዚህ አጠቃላይ አውዱ ዳዊት ሐጢአተኛ እንደሆነ በመረዳት እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው የሚለምንበት ነው።

በቁጥር አምስት ዳዊት ኀጢአቱ እጅግ እንደከበደችው እየተናገረ መጥቶ ዳዊት ሲወለድ ጀምሮ ኀጢአተኝ ነበርኩ በማለት ከዚህ በፊት እንዳየነው እግዚአብሔር በጊዜው የሚገለጥ ልብ ውስጥ ያለን የተወረሰ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ እንደሚመለከት እና ዳዊትም በእግዚአብሔር ፊት ሲወለድ ጀምሮ ኀጢአተኛ እንደነበር ይናገራል። የነገረ መለኮት መምህር ጆን ጊል ሲናገር ዳዊት ነፍሱ ከስጋው ከተዋደደበት ከዛ ግዜ ጀምሮ ሐጢአተኛ እንደሆነ ይናገራል።

ስለዚህ ዳዊት ኀጢአተኛ ተፈጥሮን ሰው በመሆን ውስጥ እንዳገኝ እየተናገረ ነው ማለት ነው።

ከዚህ በታች ግን መረዳት ያለብን ነገር ታዲያ የሰው ልብ ከሁሉ በላይ ተንኮለኛ ከሆነ ሰው በዚህ ምንባብ እንድተገለጸው ክፉ ሲሆን አይታይም ስለዚህ ይህ አስተምህሮ ከሚታየው ነገር አንጻር ትክክል አይደለም ትሉ ይሆናል። ነገር ግን ሰዎች የዚህን ክፋት ከልባቸው እንዳይወጣ የተለያዩ መከልከያዎች አሉ። እነዚህም እግዚአብሔር በአጠቃላይ ጸጋ (የጋርዮሽ) ሰዎች በትምህርት እድገት በስልጣኔ በሳይንስና በቴክኖሎጂ በስነ ጥበብ ዘርፍ ፍትህን በሚያስፈንበት በዚያ የሰዎች ክፋት እንዳይገለጥ መከልከያዎችን አበጅቷል። ልክ ሕጻኑ መልካም እንዲሆን ወላጆች እንደሚያስተምሩ እና በዚህ ምክንያት አንጻራዊ በሆነ መንገድ ልቡ ውስጥ ያለውን ክፋት መከልከያ ሆኖለታል። ሌላኛው ደግሞ በምድር ላይ እግዚአብሔር ገዢዎችን በመሾም ሰዎች ክፉ እንዳይሆኑ ፍትህ በምድር እንዲነግስ ያደርጋል ሮሜ 13፡1-7.

አንድ የሆሊውድ ፊልም በቅርብ ያየሁት ላይ በአሜሪካ በአመት የሚመጣ ቀን አለ በዚህ ቀን ለተወሰኑ ሰዐታት ሰዎች ምንም አይነት ወንጀል መፈጸም የሚችሉበት ሕግ ነበር መዝረፍ መግደል የፈለጋችሁትን አድርጉ ተባሉ በዚህ ጊዜ ምሽት ታዲያ ይህ የሰዎች ክፋት ሲገለጥ ይታያል በየመንገዱ ለመዝረፍ የወጡ ለመገደል የወጡ ብቻ ፊልሙ በዚህች ደቂቃ ውስጥ አሜሪካ እጅግ አስጨናዊ ከተማ ሆነች የተባለው ሰዓት አልፎ ሰው ሁሉ ወደ ቀደመው ሕይወቱ ሲመለስ ግን ያ ከሰዐታት በፊት የነበሩት እነርሱ አይመስሉም። ይህንን እግዚአብሔር በአጠቃላይ ጸጋ ወይም በጋርዮሽ ጸጋ ሰዎች ይህ የልባቸው ክፋት እንዳይወጣ ይጠብቃል ስለዚህም ሰዎች መልካም እና በምድራዊ ነገር ሞራላዊ ፍጡሮች ሆነው ይታያሉ ይሁን እንጂ

በእግዚአብሔር ፊት ግን ጠላቶች እንደሆን ልናምን ይገባል እንጂ በእግዚአብሔር ፊት የሆነ መልካምነት አይደለም።

# ክፍል ሦስት

## ዳግም ውልደት

የሰው ልጅ አንድ ትልቅ ችግር አለበት ይህም ችግር ኃጢአት ነው። ልቡ ደግሞ የኃጢአት ምንጭ ነው ስለዚህ ከዚህ የሕይወት መርህ የሚወጣበት እና አዲስ ልብ እንዴት ለዚህ ሰው እንደሚገጠም የምናጠናበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።

ዳግም ውልደት ከቃሉ እንደምንረዳው እንደገና መወለድ ማለት ሲሆን በሥጋ ውልደት ውስጥ በመጀመሪያ ከእናታችን እና ከአባታችን ስንወለድ በዚህ በሁለተኛው ደግሞ ከመንፈስ መወልዳችንን ለማመልከት ዳግም ውልደት ብለን እንጠራለን።

ስለዚህ በዳግም ውልደት ውስጥ አዲስ ማንነትን እና አዲስ መንፈስን እንዴት እንድመንቀበል በሰፊው እናያለን የብሉይ መጽሐፍ ምስክርነትን ተቀዳሚ አድርገን ብሉይ መጽሐፍ ስለ ዳግም ውልደት የሚለንን እናያለን።

### የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ምስክርነት

<u>**ትንቢተ ኤርሚያስ** 31፡31-36</u>

እግዚአብሔር ከአለም ሕዝቦች መካከል የመረጠው ሕዝብ ጋር ኪዳን እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ይህም ኪዳን በዘፀዓት ምዕራፍ ሃያ ላይ ተጽፎ እናገኛለን። ታዲያ በዚህ ሕግ ብዙ አድርጎች እና ብዙ አታድርጎች በሕጉ ውስጥ እግዚአብሔር ለእስራኢውል ሕዝብ በሙሴ በኩል በድንጋይ ጽላት ላይ ጽፎ በመስጠት ይህንን ኪዳን በመታዘዝ በ፣ድራቸው ሊባረኩ እግዚአብሔር ሕዝብ እነርሱ ደግሞ አምላክ ሊሆናቸው ቃል ኪዳንን አደረገ።

በሚገርም ሁኔታ ምንም እግዚአብሔር በዚህ ቦታ ለሕዝቡ ይህንን ቃል ኪዳን ያድርግ እንጂ ይህ ሕግ በአህዛብ ውስጥም ያለ ነበር።

ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ በጻፈው መልዕክቱ ውስጥ ምንም አህዛብ የተጻፈ ሕግ ባይሰጣቸውም ነገር ግን በተፈጥሮ በሕግ የሚታዘዘውን እንደሚፈጽሙ ሲናገር (ሮሜ 2፡14) ሕግ ከሚለው አስቀድሞ የገባው ውስን መስተ0ምር እንደሚያመለክተው በአውድኡ እይተወራ ያለው እግዚአብሔር በድንጋይ ላይ ጽፎ ለሕዝቡ የሰጣቸው ያው ሕግ ሕገ ልቦና ተብሎ የሚጠራው ነው።

ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚሁ መልዕክቱ እስራኤላዊያን ሆነ አህዛብ በሕጉ ፊት ሁሉም ኀጢአተኛ እንደሆነ ተናግሯል።

በዚህም ቦታ እስራኤላዊያን ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አፈረሱ ባለመታዘዝ እግዚአብሔርን አሳዘኑ እግዚአብሔርም አዲስ ኪዳን እንደሚገባ ተስፋን ደግሞ ሲሰጥ የምናነበው በዚህ ቦታ ነው።

ደግሞ የሚገባው ኪዳን አዲስ የሆነው ሌላ ሕግ ስለሆነ አይደለም ነገር ግን ያው በድንጋዩ ተጽፎ ነገር ግን ሰዎች ቃል ኪዳን ያፈረሱበት ያው ህግ ነው። ነገር ግን የሕጉ መካከለኛ እና የቃልኪዳኑ በረከት ተካፋዮች እንዲሁም ሕጉን በልባቸው የሚጻፍ መሆኑ እንዲሁም የተለያዩ በረከቶች አሉትና ይህ በረከት አዲስ ተብሏል።

በዚህ ቦታ ላይ በግልፅ እንደምንረዳው ይህ ቃል ኪዳን አሁንም እግዚአብሔር በክርስቶስ ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር እንደሆነ የሚያመላክት ነው። በዚህ ስፍራ ከእስራኤል ጋር በማለት ይኸው ኪዳን እግዚአብሔር በክርስቶስ ሕዝቤ ብሎ የጠራቸውን የራሱን ወገኖች ነው የኪዳኑ በረከት ተካፋዮች

(ዕብ 10፡16-17 8፡8-12) ።

ስለዚህ እነዚህ ሁለቱን ምንባባት አያይዘን ስንመለከት የዕብራዊያን መልዕክት ፀሐፊ ለተደራሲያኑ ያንን የተባረከ ተስፋ ለቤተ ክርስቲያን  እግዚአብሔር የተናገረው አድርጎ በመተርጎም ለአማኞች የሚጽናኑበት ሕያው ተስፋ አድርጎ ያቀርበዋል። በኤርሚያስ በኩል አዲስ ኪዳን የምገባበት ጊዜ ይመጣል የሚልበትን ይህ ኪዳን መካከለኛው ክርስቶስ ሲሆን በእርሱ በኩል ለሚያምኑ እግዚአብሔር ራሱ ሕጉን በልባቸው እንደሚጽፍ በዚህም ምክንያት ማንም ባለጀራውን እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አስተማሪ ማንም ደግሞ ተማሪ እንደማይሆን ይልቅ ሁሉንም ያው በልባቸው በሚያኖረው እግዚአብሔር በኩል እንዲሚማሩ ይናገራል።

ይህ ብቻ ሳይሆን አስደናዊው ነገር እግዚአብሔር በአዲሱ ኪዳን ያለፈው ኃጢአት ይቅር እንደሚል ደግሞም እንደማያስብ በመናገር ፍጹም የሆነ ሰላምን በክርስቶስ  በኩል ከሕዝቡ ጋር እንደሚገባ ይናገራል።

የሰው ልብ ከዚህ ቀደም ደጋግመን እንዳየነው ከሆነ የኀጢአት ምንጭ ነው አሁን ግን በእግዚአብሔር መንፈሳዊ ስራ ምክንያት እግዚአብሔርን ማወቅ እና በሕጉም መታዘዝን አገኘ።

ዘወትር ሕጉን በልባችን የሚያኖር አምላክ በመሆን ኃጢአታችንን ይቅር በማለት በክርስቶስ በኩል ለሆን ለእኛ ኩነኔያችን ያስወገደለን እኛ የእርሱ ለሆን ሕዝብ የማይገባንን ቸርነት አሳየ ማለት ነው።

ስለዚህ በእኛ የሚታይ መታዘዝ ለሕገ እግዚአብሔር ቀናኢ መሆን እግዚአብሔር ዘውትር በልባችን በመንፈሱ የሚሰራው እንደሆነ ብሉይ ኪዳን ይህንን ያስተምራል።

## <u>**ትንቢተ ሕዝቅል** 11፡19-20</u>

ከላይ ካነበብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጋር ተቀራራቢ የሆነ ነገር በትንቢተ ሕዝቄል ላይ እናገኛለን። በቀደመው ኪዳን እግዚአብሔር በእራኤል ወላዋይ ልብ እንዳዘነ በደጋጋሚ ሲገልጽ ነበር። የሰው ልብ በተደጋጋሚ ከመለወጥ ጋር ተያይዞ እየተወራ ነው። በዚህ ጥናታችን ሰዎች መለወጥ ካለባቸው ሊለወጡ የሚችሉት ልባቸው ሲለወጥ ብቻ እንደሆነ ተገንዝበናል። እግዚአብሔር ይህንኑ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለሆኑ ሰዎች እንደሚሰራላቸው ልክ ኤርሚያስ ላይ እንዳነበብነው በነቢዩ በሕዝቄል በኩል ይናገራል። ሕዝቡ ለምን ወላዋይ ሆኑ? ብለን ስንጠይቅ ምላሹ አሁንም ልብ ጋር እንደሆነ ሲናገር የስጋን ልብ ከውስጣቸው አወጣለው በማለት ዋናውን የችግሩን ምንጭ እራሱ እግዚአብሔር እንደሚያክም ይናገራል። የድንጋይ ልብ እምቢተኛ እና ለሕገ እግዚአብሔር መገዛት የማይችል ነውና ይህን ልብ ከውስጣችን የሚያወጣ የስጋን ልብ የሚሰጠን በዚህም ደግሞ ከዚያም በኋላ ትዕዛዙን መፈጸም እንደምንችል ይናገራል። ልብ እንበል ልባችንን መለወጥ እርሱ ለእኛ የሚያደርግልን እንጂ እኛ የራሳችንን ልብ የምንለውጥ አይደለንም።

በዚህ ቦታ ላይ እግዚአብሔር ምን ምን ሊያደርግልን ተስፋ እንደገባልን እናስተውል

1. ድንጋዩን ልብ ከውስጣችን ያወጣልናል
2. አዲስን መንፈስ በውስጣችን ያኖራል
3. የስጋን ልብ ይሰጠናል

በእኛ ደግሞ እግዚአብሔር ይህንን ሰላደረገልን ምን እንደምንሆን ሲናገር

1. ሕገ እግዚአብሔር እንፈጽማለን
2. ሕገ እግዚአብሔርን እንጠብቃለን
3. ለሕገ እግዚአብሔር ታዛዦች እንሆናለን
4. ሕዝቡ እንሆናለን

በእኛ መታዘዝ እና ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ በሞላ እርሱ በእኛ ውስጥ በሚሰራው አሰራር የሚሆን ነው እንጂ ከእኛ ልብ የሚወጣ አይደለም። በዚህ ቦታ የእኛ ድርሻ ኃጢአተኛ እና ወላዋይ መሆን ነው። የእርሱ ደግሞ ከውስጣችን መሰረታዊ የሆነ ለውጥን በራሱ አሰራር በልባችን ማድረግ ሲሆን በዚህም በእኛ አዲስ የሕይወት ዘይቤ መታየቱ ነው።

በዚህ ቦታ ላይ ልብ ልንል የሚገባን ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ሕጉን ይፈጽማል ማለት እንዳይደለ ነው። ነገር ግን ሕጉን ምንፈጽመው እኛ ብንሆንም ይህ ግን እግዚአብሔር በውስጣችን በመንፈሱ በኩል የሚያደርገው መሆኑን ነው።

በተለይ በዚህ ቦታ ላይ ያለውን ገለጻ በደንብ ልንረዳ ይገባል። የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ በምን አይነት ሁኔታ እያመጸ እንዳለ ለማመልከት የተጠቀመው የልባቸው ሁኔታ የድንጋይ ልብ በማለት ነው። ምንም እነርሱ ሕያው እንደሆኑ ቢመስላቸው እግዚአብሔር ግን ሕያው ሆኖ የሚመላለስ በሚመስለው ስጋዊ ፍጡር ሰው ውስጥ የድንጋይን ልብን ይመለከታል በዚህም በእግዚአብሔር ፊት ሙታን እንደሆኑ ይናገራል። አንድ ሰው በስጋ ሲኖር የድንጋይ ልብ በውስጡ ካለ በድን እንጂ በፍጹም ሕይወት ያለው አይደለም ለዚህ ነው የድንጋይ ልብ ካልወጣላቸው በፊቱ ሕያዋን ሊሆኑ እና ሕጉን ሊታዘዙ አዲስ መንፈስ ካልተሰጣቸው ደግሞ በፍጹም እንደማይለወጡ በማሰብ በምህረቱ ታላቅ የሆነ አምላክ ምንም ባይገባቸውም የድንጋዩን ልባቸውን በስጋ ቀይሮ አዲስን መንፈስ በውስጣቸው አኑሮ ለተጠሩለት እግዚአብሔርን ማክበር በእርሱም መደሰትን የተቻላቸው። ይህ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ምስክርነት ስለ አዲስ ፍጥረት መሆን የሚያስተምረው ነው።

የብሉይ ምስክርነት ዳግም ውልደታችን በእኛ ከሚታይ ፍሬያማ ሕይወት በእግዚአብሔር የሚደረግ ታላቅ የድነት ተስፋን በማወጅ ነው። ሁል ጊዜ መጥፎው ዜና ሰዎች በኃጢአታቸው እና በበደላቸው ሙታን መሆናቸው ሲሆን በዚህም የእግዚአብሔር ጠላቶች መሆናቸው ነው። መላካሙ ዜና ደግሞ ሰዎች መስራት ስላለባቸው ምንም ነገር ሳይሆን ይልቅ እግዚአብሔር በእኛ ስለሚሰራው ድንቅ ስራ ነው። ይህን የብሉይ መጽሐፍት ምስክርነት ካየን ወደ አዲስ ኪዳን ደግሞ እንሻገር።

## የአዲስ ኪዳን ምስክርነት

**ዮሐንስ 1፡11-13**

ወደ ራሱ ወገኖች መጣ በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ ወገኖቹ ወደ ሆኑት ወደ እስራኤላዊያን እንደመጣ በመናገር ይጀምራል። ኀጢአተኞች የሆኑ ሕዝቦች ግን አዳኝ የሆነውን ኢየሱስን አልተቀበሉም በማለት ይናገራል (ቁ-11) በመቀጠል ለተቀበሉት እና በስሙ ላመኑት ሁሉ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ዘንድ ልጆች የመሆንን መብት ሰጣቸው (ቁ-12) ።

እግዚአብሔር በምድር ከሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ሕዝቤ ያላቸው ተስፋ የተገባላቸው እስራኤላዊያን በኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት የመጀመሪያዎቹ ተደራሲያን ናቸው። እርሱ በዓለም ውስጥ ቢኖርም እንዲሁም ዓለምን የፈጠረ ቢሆንም ዓለም አላወቀውም ወገኖቹም አላወቁትም ነበር።

ስለ እርሱ መምጣት ቅዱሳት መጽሐፍ ቢናገሩም ቃል ስጋ ሆኖ ወደ እነርሱ ወደ ገዛ ወገኖቹ ቢመጣም አላወቁትም እንደ መሲሁ ሊቀበሉ በፍጹም አልፈለጉም ኢሳያስ በትንቢቱ አስቀድሞ እንዳመለከተው አልተቀበሉትም ይለናል ዮሐንስ በወንጌሉ (ኢሳ 53፡3) ።

መምጫው የይሁዳ ነገድ የሆነ በዳዊት ዙፋን የሚቀመጥ **ታላቅ ንጉስ** የሕዝቡን ሐጢአት ይቅር የሚል ስለ ሕዝቡም ሐጢአት በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም እንደ አሮን ያይደለ ነገር እንደ መልከጼዴቅ ባለ ሹመት **ሊቀ ካህናት** የሆነ ደግሞም ታላቁ መምህር ሕዝቡን ጥበብ በተሞላ መንገድ ሕገ እግዚአብሔርን የሚያስተምር **ታላቅ ነቢይ** እንደሚመጣ ቢነገራቸውም ጊዜው ደርሶ ቃልም ስጋ ሆኖ አልፋ እና ኦሜጋ የሆነ አምላክ እንደ ቃሉ ስጋን ለብሶ ሲመጣ ወገኖቹ ሳይቀበሉ ቀሩ በመጨረሻም አዳኛቸውን አሳድደው ገደሉትም።

ነገር ግን ከእነርሱ መካከል አንዳዶች አሉ በጌታ ኢየሱስ አምነው የተገኙ እና የተቀበሉት በዚህም የእስራኤላዊያን አለመታዘዝ ሙሉ በሙሉ አለመሆኑን እንረዳለን። ስለ እነዚህ ስለ አመኑ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ነግሮችን ይነግረናል እነዚህ ሦስት የተለያዩ ነገሮች አንድን ነገር ለማስረዳት የገቡ ናቸው።

(1) **ከደም ፈቃድ** ወይም (2) **ከሥጋ ፈቃድ** ወይም (3) **ከወንድ ፈቃድ** የሚለው አገላለጽ ምን እንደሆነ ለመረዳት ተመሳሳይ ሐሳብ የታከለበት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጋር አያይዘን ብንረዳ ሐሳቡን በሙሉዕነት እንረዳለን። ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት በተናገረበት ቦታ (ማቴ 16፡13-16 ማር 8፡27-29 ሉቃ 9፡18-20) ጌታ ኢየሱስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ጴጥሮስ ሲናገር ጌታ ኢየሱስ ይህንን ***ሥጋና ደም*** አልገለጠልህም ይላል እዚህ ቦታ ሥጋ እና ደም በአጠቃላይ ጴጥሮስን በመወከል የተነገረ ንግግር እንጂ የሚታየውን ሥጋ እና ደም አንደበት ያለው እና የሚናገር ነው ማለት አይደለም።

ስለዚህም በዮሐንስ ወንጌል ሰላመኑት ወይም ስለ ተቀበሉት ሰዎች የሚናገረው ሥጋ እና ደም ሰዎቹን በአጠቃላይ በመወከል ከእነርሱ ውስጥ ካለ የራስ ፈቃድ ሳይሆን ታላቅ አምላክ በራሱ ፈቃድ እንደወለዳቸው እና በእርሱ እንዳመኑ እንረዳለን።

እነዚህ የተቀበሉ ሰዎች አስቀድመው ዳግም ውልደትን እንደተቀበሉ ለመረዳት በ1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ምዕራፍ 5 ቁጥር 1 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ወይም መሢህ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል በማለት በገለጸው መሠረት። ዳግም ውልደት እንዴት እንደሚቀደም ለመረዳት ዓረፍተ ነገሮቹን ልብ ብለን ልንመለከት ይገባል **ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚያምን ከእግዚአብሔር ይወለዳል** ቢል ኖሮ በግልጽ የምንረዳው ነገር ቀዳሚው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማመን ተከታዩ

ደግሞ መወልድ ነበር። ነገር ግን ክፍሉ የሚለው **ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዷል** ነው የሚለን። ከእግዚአብሔር መወለድ ቀዳማይ ተግባር ወደ ተከታዩ ማመን ሰውዬውን ማምጣት በሚያመለክትበት መንገድ ከእግዚአብሔር ተወልዷል ይለናል ማን ? ብለን የጠየቅን እንደሆን ያመነው ሰው።

በዳግም ውልደት ቀዳማይ እምነት ደግሞ ተከታይ ስንል በግልጽ እንደምንረዳው ሰፊ በሆነ የጊዜ መለኪያ ውስጥ ሳይሆን በቅጽበት በሕይወታችን የሚሆን የእግዚአብሔር አሰራር ነው። አሁንም ልክ እንደ ብሉይ መጽሐፉ መቻልን የሚሰጠን በዚህም ቦታ እግዚአብሔር ነው። እርሱ በመንፈሱ አማካኝነት ዳግም ውልደትን ያከናውናል ይህም የሰዎቹ ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ወይም አስቀድመው አምነው ሳይሆን በራሱ ሉዐላዊ ፈቃድ አንዳንዶችን በልጁ በክርስቶስ እንዲያምኑ ዳግም ይወልዳቸዋል ማለት ነው።

በተለይም ደግሞ በ1ኛ ዮሐ 5፡20 ላይ **"የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ እውነተኛ የሆነውን እርሱን እንድናውቅ ማስተዋልን እንደ ሰጠን እናውቃለን እኛም እውነተኛ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አለን። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።"** በማለት የገዛ ወገኖቹ ልባቸው ባለማስተዋሉ ምክንያት እንዳልተቀበሉ ሲናገር ስለ ተቀበሉት ደግሞ ማስተዋልን የሰጠ እርሱ እንደሆነ ይናገራል። በኃጢአት ምክንያት ፍጹም ሙት የሆነው ሰው የአምላኩን ሕግ የማይታዘዝ እግዚአብሔር ጋር ጸበኛ የሆነው ሰው አሁን የእግዚአብሔርን ሕግ ታዛዥ እና የሚያስተውል ሆነ ይህም የሆነው በእግዚአብሔር ኀጢአተኛውን በሚያጸድቅበት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የድንጋዩን እና የሚያወላውለውን ልብ በማውጣት አዲስን መንፈስ በመስጠት የሥጋን ልብ በማስገባት ሕጉን በልባቸው በመጻፍ ያደረገው ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው።

## <u>ዮሐንስ ወንጌል 3፡5-8</u>

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ከፈሪሳዊያን ወገን የሆነ ከአይሁድ አለቆች መካከል ኒቆዲሞስ በጠዋት ወደ ኢየሱስ በመምጣት ከኢየሱስ ጋር ንግግር ያደርጋል። የንግግሩ መግቢያ ኒቆዲሞስ ኢየሱስ ከሚያደርጋቸው ተዓምራዊ ምልክቶች በመነሳት ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ እንደሆነ ይመሰክራል(ቁ 1-2) ጌታ ኢየሱስም ንግግሩን ሲጀምር ማንም **ዳግመኛ ካልተወልደ** በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ እንደማይችል ይነግረዋል(ቁ-3) በዚህ ንግግር ውስጥ ምን አልባት አንዳንዶች ይህ የጌታ ንግግር ትዕዛዛዊ ሊመስላቸው ይችላል (statement of command) ነገር ግን አውዱ ትዕዛዝ ሳይሆን እውነታን እየተናገረ ያለበት ነው(statement of facts)። በዚህ በጌታ ንግግር ግራ የተጋባው ኒቆዲሞስ ይህ **ዳግመኛ መወለድ** የሰው ተሳትፎ ያለበት እርሱ ራሱ የሆነ የሚያደርገው ነገር አድርጎ በመቁጠር የሰው ድርሻን እንዲህ በማለት ይግልጻል ሰው **ከሸመገለ በኋላ ወደ እናቱ ማሕጸን ሊገባና እንዲወለድ** ማለትህ ነው? መምህር ሆይ በማለት ግራ በ፣መጋባት ጥያቄውን ቀጠለ።

ጌታ ኢየሱስ አስቀድሞ እንደተናገረው አሁንም በድጋሚ ማንም ከውሃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም በማለት በመጀመሪያ የተናጋረውን ዳግመኛ መወለድ በተለየ ቋንቋ ገለጸ በእርግጥ ይህ በሁለተኛ ላይ ጌታ ኢየሱስ የተናገረበት መንገድ በቁጥር 10 ጌታ ኢየሱስ ኒቆዲሞስን አንተ መምህር ሆነህ ሳለ ይህንን እንዴት አታውቅም? በማለቱ ኒቆዲሞስ ፈሪሳዊ እንደመሆኑ ሊያውቅ የተገባው ነገር ግን ያላወቀው መሆኑን እንረዳለን። ኒቆዲሞስ ሊያውቅ የተገባው ለምንድነው? ምክንያቱም እርሱም ከፈሪሳዊያን ወገን ነውና ስለ ዳግመኛ መወለድ የብሉይ መጽሐፍት ነቢያት ተናግረው ስለነበር ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ጌታ ኢየሱስ ኒቆዲሞስን ከውሃ እና ከመንፈስ መወለድ ምን ማለት እንደሆነ ባለማወቁ ባልወቀሰው ነበር። ከዚህ ቀደም ባነሳነው ምንባብ ውስጥ አዲስን መንፈስ

እንደሚሰጣቸው በትንቢተ ሕዝቄል አይተን ነበር ስለዚህ ከውሃ እና ከመንፈስ መወለድ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ሳይሆኑ ስለ ዳግም ውልደት በእግዚአብሔር አሰራር ሰዎች የሚድኑበትን ማመልከቱ ነበር።

**በትንቢተ ሕዝቄል 36፡21-32** ባለው ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በገባው ኪዳን ውስጥ ንጹሕ ውሃ እረጫችኋለው እናንተም ንጹሕ ትሆናላችሁ በማለት ውሃን ከንጽህና ጋር በማያያዝ እግዚአብሔር ከኀጢአታችሁ አጥባችኋለው በማለት ተናግሮ ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ልክ እንደ ሕጻናት ንጹህ መሆን እንደሚገባን ተናግሯል (ማቴ 18፡3) ። መንግሥተ ሠማይ በዚህ ቦታ ከውሃ እና ከመንፈስ ከመወለድ በሚለው ኀጢአተኛውን ፍጹም ንጹህ በሚያደርግበት መንፈሳዊ ንግግር እየተናገረ መሆኑን እንረዳለን ለምሳሌ መዝሙረኛው ዳዊት በደሌን ፈጽሞ እጠብልኝ ከኀጢአቴም አንጻኝ (መዝ 51፡2) በማለት ይናገራል።ስለዚህ በዚህ ቦታ የጌታ ንግግር መንፈሳው ትርጉም ያለው ነው ማለት ነው ። ኒቆዲሞስ ግን ምን እያለ እንደሆነ በፍጹም አልተረዳም ነበር።

በመጀመሪያ ውልደታችን ስጋዊነትን ተቀብለናል በእርግጥ በእዚህ ቦታ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው የሚለውን አንዳንዶች ሥጋዊነት ወይም ኃጢአተኛ መሆን ሲሆን ከመንፈስ በመውለድ ደግሞ መንፈሳዊያን ወይንም በእግዚአብሔር ፊት ንፁህ ከመሆን ጋር አያዘው ይፈቱታል በእርግጥ የመጽሐፉም አውድም ይኸው ነው።

እንዴት ከመንፈስ ቅዱስ እንደምንወለድ ሲያስረዳ ጌታችን የተቀመው ምሳሌ ዳግም ውልደት ይቀድማል ወይስ እምነት ለሚለው ጥያቄ እጅግ ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ምን አልባትም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ከደቡብ ወደ ሰሜን ብቻ ወደ ወደደበት ይነፍሳል ማንም የንፋስን አቅጣጫ የሚመራ የለም ከዚህ የመጣ ንፋስ ወደዚያ እየሄደ ነው ሊል የሚችል የለም። እንደወደደ ይነፍሳል ይህ ሁሉ ሲሆን እኛ የነፋሱን ተጽእኖ እናስተውላለን አሁን ይሞቃል፣ አሁን ደግሞ ነፋሻማ ነው፣ አሁን ይበርዳል በማለት ውጤቱን እየተመለከትን ከምንመለከተው ነገር በስተጀርባ ያለን እውነት እንናገራለን።

ከመንፈስ የሚወልድም እንዲሁ ነው አለ ጌታችን መንፈስ ቅዱስ ወደ ወደደው ይነፍሳል እርሱ ፍጹም ሉዐላዊ አምላክ ነውና ወደዚህ ንፈስ ወደዚያ ደግሞ ንፈስ አይባልም ነገር ግን ሰዎች ከመንፈስ ቅዱስ መወልዳቸውን ከመነፍስ በሆነው ፍሬ እናውቃቸዋለን። አንድ ሰው እምኖ ዳግም ይወለዳል የምንል ከሆነ በእዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በፍጹም እየተጣረሰ ነው። አበበ የሚባል ሰውዬ በወንጌል ጥሪ ሲያምን እኛ ደግሞ በቃ አበበ ዳግን ሊወለድ ነው ብለን መገመት እንችላለን። ይህ ግን ትክክል አይደለም መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እምነት እና ንሰሀ የእግዚአብሔር ስጦታ (መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን በመሆን የሚቸረን) ነው እነዚህን ሁለቱን ነገሮች እንመልከት።

በፊሊጵስዩስ ለሚገኙ ወንድሞች በተጻፈ መልዕክት ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞችን መከራ እንዲቀበሉ ሲያበረታታ እንዲህ በማለት ተናግሯል

**ፊል 1፡29 "ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና ስለ እርሱ መከራ እንድተቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም"**

የፊሊጵስዮስ ወንድሞች በጳውሎስ አነጋገር እምነትን እግዚአብሔር የሰጣቸው በእርሱ እንዲያምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራም እንዲቀበሉም ጭምር ነው ማለት ነው።

እንዲሁም ስለ ንሰሀ ደግሞ ጢሞቲዮስን ስለሚቃወሙ ጠቃዋሚዎች ጢሞቲዮስ ምን አይነት ልብ ሊኖረው እንደሚገባ ሲመክረው እንደዚህ በማለት ነው።

**2ጢሞ 2፡25-26 "ደግሞም ምን አልባት እግዚአብሔር እግዚአብሔር እውነትን ያውቁ ዘንድ ንሰሐን ይሰጣቸዋልና ፈቃዱን ለማድረግ በዲያቢሎስ ሕያዋን ሆነው ከተያዙበት ወጥተው ወደ አእምሮ ይመለሳሉ ብሎ በየዋህነት የሚቃወሙትን ይቀጣ።"**

ታዲያ ለእግዚአብሔር ሙት የሆነው ለዲያብሎስ ደግሞ ሕያው ሆኖ የታሰረ የሰይጣን ተገዢ ሰውን እንዴት ነጻ ነው ልንል እንችላለን? ታዲያ ነጻ ካልሆነ አስቀድሞ ከሙታን መካከል ሊቀሰቅስ የተገባው አይደለምን? እምነትን እና ንሰሐ እግዚአብሔር ሲሰጥ ሰዎች ወደ እምነት ይመጣሉ። በዮሐንስ ወንጌል ላይ ያለውን ስናጠቃልል ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሰዎችን በመንፈሱ ዳግም ሲወልድ መንፈስ ቅዱስ በራሱ ፈቃድ ወደ ወደደው እየነፈሰ የወደደውን ዳግም እይወለደ ወደ እምነት በማምጣት ንሰሐ እንዲገቡ በውስጣቸው የሚሰራው እራሱ እግዚአብሔር ነው ይህንንም ዳግም ውልደት ብለን እንጠራለን ነው።

መንፈስ ቅዱስ ዳግም ውልደት ሲያከናውን የማንገነዘበውና በሰውኛ እንዲህ ነው የምንለው ነገር አይደለም ነገር ኃጢአተኛው በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቅ የምንገነዘበው ነው ማለት ነው።

ስለዚህ ምክንያት እና ውጤት አድርገን የምንረዳው ነገር ምክንያቱ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ውጤቱ ደግሞ ኃጢአተኛው በእውነተኛ ንሰሐ እና እምነት መምጣቱ ነው።

## **ኤፌሶን** 2፡4-6

በአዲስ መደበኛ ትርጉም በክርስቶስ ሕያው መሆን በሚል ኀይለ ቃል የሚጀምረው ምዕራፍ ሁለት ከቁ 1 እስከ 10 ያለው ሲሆን ይህንኑ መልሰን ደግሞ ሁለት ቦታ ከፍለን ልንረዳ የምንችለው ነው። የመጀመሪያ መደብ በክርስቶስ ሕያው ከመሆናችን በፊት ስለነበርንበት ሁኔታ ሲሆን ይህም ከቁ-1 እስከ ቁ-3 ነው ቀጥሎ ደግሞ እንዴት ባለ ታላቅ ምህረት እግዚአብሔር እንዳዳነን የሚናገርበት ክፍል የሚገኘው ከቁ-4 እስከ ቁ-10 ድረስ ነው።

በመጀመሪያው መደብ ውስጥ በበደላችን እና በኀጢአታችን ሙታን እንደነበርን ይናገራል በዚህ ቦታ የሚያወራው መንፈሳዊ ሙትነትን ነው። መንፈሳዊ ሞት ማለት እኛ ከኀጢአታችን እና በበደላችን የተነሳ የነበርንበት ሁኔታ እና ከእግዚአብሔር ጋርም ያለንን ግንኙነት አጠቃሎ የሚይዝ ነው። በቁጥር ሁለት የዓለምን ክፉ መንገድ ስንከተል የማይታዘዙትን ለሚገዛው በእነርሱ ውስጥ የሚሰራው ያው መንፈስ በእኛ ይሰራ የነበርን ልክ እንደነሱ እኛም በዚህ ምክንያት የቁጣ ልጆች የነበርን ነበርን።

እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት በማለት ጳውሎስ ከመዳናችን በፊት የነበርንበትን ሁኔታ ሲያስታውስ በእነዚህ እግዚአብሔርን በማይታዘዙ ሰዎች መካከል የሥጋችንን ምኞት (የሥጋ ስራ ገላ 5፡19-21) በእርካታ ወይም ደስታ እያገኘንበት የኖርን ሰዎች ነበርን ይላል።

ሙታን በነበርንበት ወቅት በእኛ እና እግዚአብሔርን በማይታዘዙ ሰዎች መካከል ምንም አይነት ልዩነት እንደሌለ መረዳት አለብን እኛም እንደነርሱ እነርሱም እንደ እኛ ሁላችንም የቁጣ ልጆች ነበርን እነርሱን የሚገዛው ያው መንፈስ እኛን ይገዛን ነበር ታዲያ እኛ ከእነርሱ ለእግዚአብሔር የተሻልን ነበርን? በፍጹም እኛም እንደነርሱ የቁጣ ልጆች ነበርን።

ታዲያ በእነርሱ መካከል ባለመታዘዝ ስንመላለስ የነበርነውን እኛ በቁጥር 4 አስደናቂ ፍቅሩን ገለጠልን እንዲህ በማለት ሐዋርያው ይገልጸዋል **"ነገር ግን በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደድን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ"** ሙታን የነበርነውን ሕያዋን አደረገን። በበደላችን እና በኀጢአታችን ሙታን መሆን በፍጹም ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ነው በሰይጣን ባርነት ውስጥ የእርሱን ፈቃድ መፈጸም ነው። ሕያው መሆን

ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ነው። ታዲያ በወንጌል ለእምነት እና ለንሰሀ የሚደረግን ጥሪ ታዛዦች የሆነው እርሱ ሕያዋን ስላደረግን ነው። ይህ እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ያደርገው ነው እንጂ ሙት ከሆነው ሰው የወጣ መታዘዝ በመሆኑ አይደለም። ሲያጠናክር በእምነት በጸጋ ድናችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ይላል። እግዚአብሔርን መታዘዝ ከየት አገኘን እርሱ ሕያው አድርጎን ነው።

ስለዚህ አስቀድሞ እግዚአብሔር ሕያው ሳያደርገን በፍጹም እኛ እርሱን ልንታዘዘው አንችልም ማለት ነው።

**<u>ማጠቃለያ</u>**

እውነተኛ ንሰሐ እና እምነት የእግዚአብሔር በመንፈሱ አማካኝነት በልባችን የሚሰራው ስራ ነው ስንል አንዳንዶች እኛ ንስሀ ካልገባን ንስሀችን ትክክል አይደለም የሚል ተቃውሞ ያነሳሉ ይህ ግን የእኛን ሀሳብ በአግባብ ካለመረዳት የመነጨ ነው። ከእምነት ዳግም ውልደት ተቀማይ ነው ስንል ኀጢአተኛን ሰው ወደ እውነተኛ ንሰሀ የሚመራው እግዚአብሔር መሆኑን እንጂ እግዚአብሔር በሰውዬው ውስጥ ንስሀ ይገባል እያልን አይደለምወይም ደግሞ ለእኛ ያምንልናል ማለትም አይደለም ነገር ግን እምነትን በልባችን በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ድንጋዩን ልባችንን ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር ነገር ድንጋይ የሆነውን ልባችንን በመንፈሱ ይለወጥና የእግዚአብሔርን ነገር እንድናውቅ የንሰህን ጥሪ እንድንቀበል ያደርጋል።

ይህን ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ በጻፈው ሁለተኛ መልዕክት ምዕራፍ 4 ቁጥር 3 ጀምሮ እስከ 6 ባለው ሲናገር ወንጌላችን ለሚጠፉት የተከደነ ሲሆን የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን የወንጌሉን ብርሃን እንዳይመለከቱ ልቡናቸው በማሳወሩ ምክንያት የወንጌሉን ብርሃን ሊመለከቱ አልቻሉም ይለናል። የወንጌሉን ብርሃን እንድንመለከት ጨለማን ልባችን ላይ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነው ይለናል። እግዚአብሔር ብርሃኑን ባያበራ ኖሮስ ? ልክ እንደሚጠፉት ጠፊ ከመሆን ውጪ ምንም ተስፋ አይኖረንም ነበር ነገር ግን በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደቀን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ብርሃኑን አበራብን ወደ እርሱም መምጣት ቻልን።

2ጢሞ 1፡9 **“እኛ ስላደርግነው አንዳች ነገር ሳይሆን ከዕቅዱና ከጸጋው የተነሳ ያዳነን ወደ ቅዱስ ሕይወትም የጠራን እርሱ ነው ።”**

መዳናችን አንዳች እኛ ሰላደርግነው ነገር አይደለም ነገር ከእርሱ ዘላለማዊ እቅድ የተነሳ ነው። ደግሞም ወደ ቅዱስ ሕይወትም የጠራን እርሱ ነው። ስለ እምነቴ ነው አንልም ምክንያቱ አንዳች እኛ ስላደርገነው አይደለም ነገር ማመናችን ወደ እርሱ መምጣታችን ከዕውዱና ከጸጋው የተነሳ ብቻ ነው።

እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በተጨማሪ ይመልከቷቸው [ቲቶ 3፡5 ያዕ 1፡18 1ጴጥ 1፡23 1ኛ ዮሐ 3፡9]

# ክፍል አራት

## እግዚአብሔር አድልዎ ያደርጋልን?

እግዚአብሔር አድልዎ ያደርጋልን? ይህ ሐረግ የሚገኘው በሮሜ 9፡14 ላይ ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሉዐላዊ ምርጫ በሚያስተምርበት ወቅት ተደራሲያኑ ሊጠይቁ የሚችሉትን ራሱ ያነሳው ጥያቄ ነው። እግዚአብሔር ያዕቆብን ወደደ ዔሳውን ጠላ ይለናል ቁ-13 ታዲያ በዚህ ንግግር ውስጥ እግዚአብሔር አድልዎ ያደርጋልን? በማለት ጠይቋል መልሱንም በግልጽ **በፍጹም አያደርግም!** በማለት ይመልስዋል። ሁለተኛው የሚነሳው ጥያቄ ደግሞ ታዲያ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅዱ ይህ ከሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማን ሊቋቋም ይችላል? ይህ ከሆነ ደግሞ ለምን ይወቅሰናል? ብለው እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን በመቅጣቱ ጻዲቅ እንዳልሆነ ሊያስቡ እንደሚችሉ ቅዱስ ጳውሎስ በመረዳት ለዚህም የሚሰጠን መልስ ሥራ ሠሪውን ለምን እንዲህ ሠራኸኝ ሊለው ይችላል? በማለት መልሶ ይጠይቃል ሸክላ ሠሪ ከሚሠራው ጭቃ አንዳንዱን ሸክላ ለክብር ሌላውን ደግሞ ለተራ አገልግሎት የማድረግ መብት የለውምን? በማለት ጥያቄን በጥያቄ ይመልሳል ሥራ ሠሪውን ለምን እንዲህ ሠራኸኝ ሊል አይችልም ሸክላ ሠሪውም ባለ ሙሉ መብት ነው።

ነገር ግን ለምን ብለን ብንጠይቅም መሠረታዊ የሆነ ነገርን ስተናል ምክንያቱም የእኛ ጥያቄ ዔሳውን ለምን ጠላ ነው ? ነገር ግን ሌላኛው ያልተመለሰ ጥያቄ ዔሳውንስ ለምን ወደደ? ይህንን መልስ ስንመልስ ብቻ እግዚአብሔርን የጽድቅ ጥያቄ ልንጠይቅ የምንችለው። ይህንን እኛ አናውቅም ጳውሎስም የእግዚአብሔር ሐሳብ በምርጫ ይጸና ዘንድ ነው ብሎ ይመልሳል (ቁ-11) እንጂ ሐሳቡን አያሳውቅም። የእግዚአብሔርን ሐሳብ ልትመረምር ለመሆኑ አንተ ሰው ሆይ ማን ነህ? አንተ የእጁ ሥራ የጥበቡ ቅንጭብ ማሳያ አይደለህምን? ታዲያ እንዴት ይህንን ልትመረምር እና ልትደርስበት ትችላለህ?

**“የእግዚአብሔር ጥበቡ እና የዕውቀቱ ባለጠግነት እንዴት ጥልቅ ነው! ፍርዱ አይመረመርም ለመንገዱም ፈለግ የለው...” ሮሜ 11፡33**

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በጸጋው ከሰዎች መካከል መርጦ እንዳዳነን በሚናገሩ ቦታዎች ሁሉ ከምስጋና ጋር እንጂ በፍጹም አማኞች ባዳናቸው እግዚአብሔር ላይ እግዚአብሔርን ስለ ምርጫው እና ስለ አሰራሩ በማጉረምረም እንዲያስቡ በመጋበዝ አይደለም። ለምሳሌ ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልዕክት በመንፈሳዊ በረከት ተባርካችኋል በማለት ሲናገር ከዚህ ምርጫ ውስጥ አንደኛ ዓለም ሳይፈጠር መመረጣቸው እና በክርስቶስ ሥራ ደግሞ ልጆች እንዲሆኑ መወሰኑም ነው። በተጨማሪም ለተሰሎንቄ በጻፈው ሁለተኛ መልዕክት (2ተሰ 2፡13) ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እነርሱ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን የሚናገረው ነገር “እግዚአብሔር እናንተን ከመጀመሪያ አንስቶ በመንፈስ ተቀድሳችሁ በእውነትም አምናችሁ እንድትድኑ መርጧችኋል በማለት ነው።”

ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ መመረጣችንን እየተናገረ እግዚአብሔርን ማመስገን ሲያመጣ ምነው አርሚኖሳዊያን ግን የለም እግዚአብሔር አዳላ አሉ?

ደግሞ መሠረታዊው እውነታ በመጨረሻው ቀን በፍርድ ፊት ማመካኛ እንደማይኖራቸው ነው። ሁሉም እንደየሥራው መቀበሉ ነው። ማንም የማይገባውን ፍርድ እንደተቀበለ ሳይሆን ኀጢአተኞች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን የወደዱ ክፋትን የሚያደርጉና ወደ ብርሃን የማይመጡ ሲሆን የሚፈረድባቸውም በዚህ ምክንያት ነው (ዮሐ 3፡18-20) እንዲሁም ደግሞ ብርሃንን የወደዱ እና በእውነት የተመላለሱ እነርሱ

ሥራቸው በእግዚአብሔር የተሠራ መሆኑ በሰዎች ሁሉ ፊት እንዲታይ ወደ ብርሃን ይመጣሉ (ዮሐ 3፡21)። ኀጢአተኞች የሚገባቸውን ፍርድ ሲቀበሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ዓለም ሳይፈጠር የመረጣቸው በመንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለዱት ደግሞ ጸጋን ተቀበሉ ማለት ነው።

እኛ በክርቶስ ኢየሱስ ኢየሱስ የተመረጥን ሰዎች ካልተመረጡት በምንም የተለየን አልነበረም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርድን እንዳንቀበል የሚያደርግ ምንም መልካም ሥራ አልነበረንም። ከእግዚአብሔር ጋር ጠላቶች የነበርን ነን በእግዚአብሔር ፊት ከኀጢአታችን ውጪ ምንም አልነበረንም ልክ እንደ ሌሎች የእኛም ልብ ተንኮለኛ የኀጢአት ምንጭ ነበር ታዲያ ከዚህ ዘላለማዊ ፍርድ ማምለጣችን ከእኛ በሆነ ሳይሆን በእርሱ ጸጋ መሆኑ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ምርጫን ከምስጋና ጋር አያይዞ የሚያቀርብበት ምክንያት። ለእኛ እግዚአብሔር ጸጋውን ገለጠ ላለመረጣቸው ደግሞ ፍትህን አደረገ። እኛ ያልተገባንን በልጁ በክርስቶስ እንደራሱ ዕቅድ መሠረት መርጦን ልጆቹ አደረገን ሊመጣ ካለው ቁጣ አመለጥን።

ሰው ሁሉ ኀጢአትን ሰርቷል (ሮሜ 3፡23) እግዚአብሔር ሰው ሁሉ ላይ መፍረድ እና ሰውን ሁሉ ሲያል ማስገባት መብት የለውምን? አለው ምክንያቱም የኀጢአት ደሞዝ ሞት ነውና። ነገር ደግሞ አሁንም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ሁሉንም ይቅር ብሎ ማዳን ቢፈልግ መብቱ አይደለምን? ይችላል ምክንያቱም ምህረት የራሱ ገንዘቡ ነውና። እግዚአብሔር ግማሹን በክርስቶስ ሥራ ይቅር በማለት ግማሹን ግን ስለ ኀጢአቱ መቅጣት መብት የለውምን? ይችላል ምንም ጣቄ አያስፈልገውም።

በዚህ ሁሉ ሰው ከእግዚአብሔር ምንም አይነት የይገባኛል ነገር ውስጥ መግባት አይችልም። ታዲያ ከዚህ ውስጥ የሆነው የመጨረሻው ነው እግዚአብሔር ቁጣውን ለማሳየት ወዶ አንዳንዶችን አልመረጠም እግዚአብሔር ምህረቱን ሊያሳይ ወዶ አንዳንዶችን መርጧል እኛ ከተመረጡት የሆን ታዲያ ምን አይነት ታላቅ ድነት እንደሆነልን ልናስተውል ይገባል።

አንድ የኢንግሊዘኛ መዝሙር አለ እስቲ ግጥሙን ተመልከቱ

Amazing Grace, how sweet the sound
That saved a wretch like me
I once was lost, but now am found
Was blind but now I see

Was Grace that taught my heart to fear
And Grace, my fears relieved
How precious dis that Grace appear
The hour I first believed

Through many dangers toils and snares
We have already come
T'was Grace that brought us safe thus far
And Grace will lead us home
And Grace will lead us home

Song writer John Newton

ጥያቄ ለአርሜኖሳዊያን

1.የተሀድሶአዊው እምነት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተቀባይነት ያለው መሆን ግልጽ ነው ታዲያ እናንተ አሁን ያላችሁበት አቋም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የማያቀው እንግዳ ውግዝ የሆነውን ነው ታዲያ እናንተ አባቶች ያልተቀበሉት ተቀብላችሁ ስትኖሩ ኦርቶዶክሳዊ (ቀጥተኛ) ነኝ ብላችሁ እንዴት ታምናላችሁ?
2.መጽሐፍ ቅዱስ መመረጣችንን ከምስጋና ጋር ሲያቀርብ እናንተ ግን የምርጫን ሆነ የዳግም ውልደትን ሥራ እንዴት እግዚአብሔር አድልዎ ያደርጋል ትላላችሁ?
3.ያዕቆብን ለምን እንደወደደ መልስ ሳይኖርህ ዔሳውን ለምን ጠላ ብለህ መነሳትህ ከአምክንዮ ሕግ ጋር መጣረስህ አይደለምን? ስለማታውቀው ነገር እንዴት ስህተት ወይም ትክክል ብለህ ብያኔ ትሰጣለህ?
4.አብ ካልሳበው ማንም መምጣት አይችልም (ዮሐ 6፡44) ይህ ምን ማለት ነው?
5.እምነት እና ንሰሀ የእግዚአብሔር ስጦታዎች (ፊሊ 1፡29 ኤፌ 2፡8-9 2ጢሞ 2፡25-26) ከሆኑ ታዲያ ሰዎች በራሳቸው ማመን ይችላሉ ማለት ይቻላል?
6.ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አብ የሚገልጠው ከሆነ ይህም የድነታችን መሠረት የኢየሱስን ክርስቶስ ማንነት ማወቅ ከሆነ ታዲያ እንዴት አብ ካልገለጠ እኛ በራሳችን እንችላለን ማለት ይቻላል?
7.መጽሐፍ ሁሉ ከእርሱ ደግሞም በእርሱ ለእርሱ ነው ይላል (ሮሜ 11፡36) ታዲያ ይህ ድነታችንን በተመለከት ጳውሎስ የሚናገረው መዳናችን ከእርሱ በእርሱ ደግሞ ለእርሱ ክብር ነው ማለት አይደለን?
8.ለመሆኑ የሞተ ሰው እንዴት ከሙታን ሳይነሳ ሊያምን ይችላል?
9.የሞተ ሰው እራሱን እንዴት ሕያው ያደርግ ዘንድ ይችላል?
10. የተቀበሉት ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ ማለትም በእነርሱ ሆነ በአላጆቻቸው ፈቃድ አልተወለዱም ይለናል (ዮሐ 1፡13) እናንተ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሰውዬውን አስፈቅዶ ነው የሚወልደው ትላላችሁ አይጣረስምን?

## ውዳሴ

**ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን ከምሕረቱ የተነሳ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤ ይህንም መንፈስ እግዚአብሔር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ አትረፍርፎ አፈሰሰው፤ ቲቶ 5፡5-6**

(Email) Amanuelendale223@gmail.com (telegram) @Amani_reformed (fb) Amani endale golfa bocm

ዋቢ መጽሐፍት

1. Reformed faith - Loraine Boettner
2. Chrstian Thelogy part two - Erickson
3. Practical view of Regeneration - Archibald Alexander
4. Hamartiology - Dr. Robert D. Luginbill
5. Systematic theology - Dr. Wayine Grudem
6. Gill's Bible Commentary - John Gill
7. A plan of salvation - Professor Benjamin B. Warfield
8. Saved by Grace- John Bunyan
9. Five Points - Dr. John Pieper
10. Systematic Theology - Louis Berkhof
11. The Lord's Day-Sam Waldron
12. Historical Theology - William Cunningham
13. Divine Covenants - Arthur W. Pink
14. Discourses on God's Salvation of Sinners-Stephen Charnock